# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅፅ 33 ቁጥር 4 ጥር 10 2000 ዓ.ም


## ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨቋኝ ሥርዓቶችና ገዢዎች ሲፈራረቁበትና የባዕድ ወራሪዎች ሀገሩን ሊቀሙት ሲዘምቱበት ሰለቸኝ መረረኝ ሳይል አስፈላጊውን መሥዋዕት እየከፈለ ታግሎ መዋጋት ያለበትን ጦርነቶች ሁሉ በጀግንነት ተዋግቷል:: ጦርነት እንሠራለን፤ እንሰራብሃለን ብለው የደነፉበት ከንቱዎች ቀርቶ ማንም ሆነ ማን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ጦርነት አስከፊነት ገለጣ ሊሰጠው አይችልም:: ባፈሰሰው ደምና በተቀበለው መከራ ለሌሎችም ስለ ጦርነት ምንነት ትምህርት ሊሰጥ ስለሚችል ነው::

ልቡ ከቂም በቀል፤ቃሉ ከመበደልና እጁ ከመግደል ያልታቀበው ጨቋኝ ቡድን ሆነ ጭፍሮቹ ነጋ ጠባ በየአቅጣጫው የጦርነትን ነጋሪት እየጎሰሙ እያለ ስለ ሰላም ወሳኝነትና ስለ ጦርነት መጥፎነት ሲያወኩ ጆሮን ሰጥቶ መገኘቱና አልፎም ለማመን መከጀሉ ተላላነት መሆኑ ግልፅ ነው:: የቀበሮ ባህታዊ የበግ ለምድ ያጠልቃልና ይህ የግፍና ጦርነት ቀፍቃፊ የሆነው አገዛዝ ሰላም ሰላም ሲል ሕዝብ እጁን አጣጥፎና ትጥቅ አልባ ሆኖ እንዲገዛለት መሆኑን ማወቅ ግዴታ ነው:: በ1983 ዓ.ም. ወያኔ ለሥልጣን ሲበቃ ለዚሁ ቦታ ያደረሰውን ጦረኝነት በራሱ ላይ እንዳይመጠባት በሚል ሰላም ብቻ ብሎ ሲለፈፍና አልፎ አልፎም ሞክሩኝ የጦርነት ግን ሰሪ እኔ ብቻ ነኝ ብሎ ሲደነፋ ሰምተናል:: ይህን የሀሰት ልፈፋውን ያጀቡለት ና የሽግግር ጉባዔ በሚለውም ተኮልኩለው የዘረኝነት ጠባብ መርዙን አብረው ሲረጩ የነበሩ የሰላም አባወራዎች ነን ባዮች ጥቂቶች አልነበሩም:: ወያኔም መሠረቱና ልቡ ሁሉ በደምና በጦርነት ላይ መሆኑን ሊሸፍን ደፋ ቀና ሲልና የባዕዳን ገደል ማሜቴዎችንም ይዞ ታጋይ ኃይሎችን በጦረኝነት ሲከስ ሐቅ ነው ብለው ምስክር የሰጡ ዛሬ የወረወሩትን ቃል በቃሊቲም፥ በስደትም፥ በሞትም መልክ መልሰው መቀበል ሲገደዱ መታዘባችንም አልቀረም:: ወያኔና ሰላም ትላንትም ዛሬም ሆድና ጀርባ፤ የማይታረቁ ጠላቶች መሆናቸውን ማንም ሊስትና ሊክድ አይገባውም::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሌም ለሰላም ጆሮውን እየሰጠና ሰላም ልናመጣ ለሚሉትም ልቡን እየለገሰ በትዕግስት ቢጠብቅም ያገኘው ውግረትንና ዳግም ጦርነትን መሆኑ በታሪክ የታየ ሐቅ ነው፡፡ የደርግ አገዛዝ ሳይውል ሳያድር የሕዝብን መብት አፈር አብልቶ አሰቃቂ ሽብርና ጦርነትን በማስፈን የብዙ መቶ ሺ ዜጋን ሕይወት አጠፋ፡፡ ብዙ ሺዎችን በአሰቃቂ ስየል ጠብሶ ለዘላለም አቆሰለ ፡፡ አረመኔው አገዛዝ የደም ግብርን በጠየቀ ትግል ሲወድቅ የተካው የደደቢት መንጋ በበኩሉ ለሰላም ቆሚያለሁ ብሎ ተናግሮ ሳይጨርስ፥ አገዛዙን በንፁኃን ደም ጎርፍ ሊያጥብ ሊገነባ መነሳቱን አሳየ ፡፡ ሊያብሩና ሊስማሙት የሞከሩትን ሳይቀር በተራ ተራ መነጠረ ፡፡ ይህ ብዙ ሺ የፖለቲካ እስረኞችን አፍኖ ያለ አገዛዝ ከአዲስ አበባ ተማሪዎች እስከ አረካ፣ ከአንዋር መስጊድ እስከ አደባባይ ኢየሱስ፣ ከወተር እስከ አርባጉጉ፣ ከጋምቤላ አስከ ኦጋዴን እየፈጀና እየጨፈጨፈ ግን በግልባጩ ድርቅ ብሎ የሰላም ሥርዓት ሰፍኗል፣ ፀረ ሰላሞችን እየተዋጋን ነው ወዘተ... እያለ በመለፈፍ ላይ መቆየቱ ደግሞ በሕዝብ ሁሉ የታወቀ ነው፡፡ በቃሉ እንፈትነው ብለው በዕርቅና ሰላም መንገድ ሊወስዱት የፈለጉትንም በዕብሪት ዞር በሉ ከማለቱ ሌላ ወደ እስር ቤትም ከቷቸዋል፡፡ ሰላማዊ ትግል በቃል ደረጃ ተወስኖ ግን በገቢር በዚሁ መስክ ሊሰማሩ የሞከሩትን ሁሉ በአፈና ቀጥቷል፡፡ በግንቦት 1997 የተካሄደው የምርጫ ውድድርና የተከተለው ፍጅት የወያኔ አገዛዝ መቸም ቢሆን መቸ ለሰላምና ለሕዝብ ውሳኔ ድምፅ ተገዢ እንደማይሆን አረጋግጧል፡፡ ይስበረኝ ይሰንጥረኝ የሚሉ የሰውን ልብ ሊሰብሩ እንደተባለው ሁሉ ሰላም ሰላም የሚሉት አረመኔዎች ሕዝብን ትግል ተው ብለው በሰላም ስም አጨምተው በባርነት ሊገዙ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡

የወያኔ አገዛዝን በሰላምና ዕርቅ ጎዳና ለመውሰድ ብዙ ሙከራዎች ተደርገው እንደተጠበቀው በአገዛዙ ግትርነት ከሽፈዋል፡፡ በሀገራችን ባህል የተጣላን ማስታረቅ የተለመደ ቢሆንም በፖለቲካው መስክ የዕርቅ ፅንሰ ሀሳብ ሁሌም ሲውጠነጠን በተለይም ከፈረንሳይ የመጀመሪያው አብዮት ጀምሮ ያለውን ሥርዓት ከውድቀት ለማዳንና ለመጠገን እንደነበር የተመዘገበ ነው፡፡ በመሠረታዊ ጥቅምና ፍላጎት የተቃረነን ሕዝብና ሥርዓት ወይም አገዛዝ ማስታረቁ ከባድ ከመሆኑ ሌላ ዕውን የመሆኑ ሁኔታ በጥያቄ የሚገባ ነው፡፡ በመለስተኛ ደረጃና በዋና ደረጃ ያሉ ቅራኔዎች ለየቅል ናቸው፡፡ በሕዝብ መሀል ያሉ ቅራኔዎችና ልዩነቶች ሁሌም ቢሆን መለስተኛ ናቸውና ሊታረቁ ይችላሉ፡፡ ወያኔ ሲመሠረት ጀምሮ በሕዝብ መኃል ያሉ ቅራኔዎችን የመጀመሪያ ደረጃን ሰጥቶ የኢትዮጲያ ብሔረሰቦች ያለው ቅራኔ የማይታረቅ ነውና ሁሉም ብሔረሰብ ተገንጥሎ የራሱን ነፃ መንግሥት ማቋቋም አለበት ከማለቱ በተጨማሪ ይህን የሚቃረኑ ሁሉ የሸዋ ትምክህተኞች ናቸው በሚል ደምድሞም ነበር፡፡ ይህን ጠባብና ጎጂ አቋም ገና ብቅ ሲል ኢሕአፓ ያጋለጠውና የታገለው ቢሆንም ወያኔ ለሥልጣን ሲበቃም በሽታው አልለቅ ብሎት ሕዝብን ማጋጨቱና ሀገርን መከፋፋሉ ሥራው ሆኖ ይገኛል፡፡ በአንፃሩ በሰፊው ሕዝብና በሥርዓቱ ወይም በገዢው ክፍል መሀል ያለው ቅራኔ ማለትም በኢትዮጵያ ሕዝብና በወያኔ አገዛዝ መኃል ያለው ቅራኔ የሚታረቅ አይደለም፡፡ በአንዱ ወይ በሌላው አሸናፊነት ብቻ ሊፈታ የሚችል ቅራኔ ነው፡፡ የወያኔ አገዛዝ ፀረ ዴሞክራሲ ነው--ሕዝብ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ

*መብቱን መጎናፀፍ ይፈልጋል። የወያኔ አገዛዝ ጠባብና ዘረኛ ነው። ሕዝብ ደግሞ በእኩልነት በጋራ ና በአንድነት መኖርን ይመኛል። የወያኔ አገዛዝ በሕግ የበላይነት አያምንም--ሕዝብ በሕግ የበላይነት ያምናል። ወያኔ ኢትዮጵያን ማዋረድና መከፋፈል ተልዕኮው ነው። ሕዝብ ደግሞ ውድ ሀገሩን የሚነካበትን በጠላትነት ይዋጋዋል። የወያኔ አገዛዝ ለባዕድ ያደረ ቅጥረኛ ነው--ሕዝብ ደግሞ በሀገሩ ሉዓላዊነት አይደራደርም። ወያኔ በዝባዥ ነው--ሕዝብ ከብዝብዛ ነፃ መውጣትን ይፈልጋል። በሀሉም መስክ የወያኔ አገዛዝና ሕዝብ የተቃረኑ ናቸው። በዕርቅ ሊሸጋሸጉ አይችሉም፥ አንዱ ለሌላው እጅ እስካልሰጠ ድረስ። ሕዝብ ለጨቋኝ ገብሮ ሀገሩን በውዴታ ያጣል የሚለው የሚታሰብ አይደለምና ሕዝብና ወያኔ ሊታረቁ የሚችሉ አለመሆናቸው ግልፅ ይሆናል።*

*ወያኔ ሥልጣን ጨብጦ እስካለ ድረስ ከሥልጣን የተወገደ ኃይልን በምናይበት መነፅር ልናየው አንችልም። በደቡብ አፍሪካ ዘረኛው የነጮች አገዛዝ ሲወድቅ የሐቅና የዕርቅ ሂደት በሚል ዘረኞቹ ሳይቀጡ የታለፉበት ሁኔታ ዛሬ ጠቃሚነቱና ትክክለኛነቱ በጥያቄ እየገባ ከመሆኑ በላይ ሂደቱ የተከናወነው ዘረኞቹ ከሥልጣን ተወግደው፤ የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ተፈተውና የአፍሪካውያኑ ድርጅት ኢ ኤን ሲ በምርጫ ሥልጣንን ይዞ ከተገኘ በኋላ ነው። ወያኔ ሥልጣን ይዞ ሕዝብ ሥልጣን ተነፍጎ የሚካሄድ የዕርቅ ሂደት ሊኖር አይችልምና የተሞከሩት ሁሉ ከሽፈዋል። የኃይል ሚዛን ጥያቄ መነሳቱም አይቀርም። አንዱ ቆሞ አንዱ ተንበርክኮ ባለበት ሁኔታ ዕርቅ ሳይሆን መጎንበስና እጅ መስጠት ነው የሚከሰተው። በመሆኑም በቅርቡ በሀገራችን ራሳቸውን አስታራቂ ሽማግሌዎች ብለው ሰይመው በተጨባጭ እጅ አሰጪ ና አስጎንባሽ የሆኑት ግለሰቦች ከዚህ ሌላ ሚና ሊኖራቸውም የሚችል አልነበረም። ዛሬም ተቃዋሚ ኃይሎችን እየተገናኙ ለወያኔ አገዛዝ እጅ ስጡ ብለው መስበካቸውም የሚያስገርም አይሆንም። ወያኔ በሥልጣን እስካለ ድረስ ከሕዝብ ያለው ቅራኔ የማይታረቅ ነው። ከሥልጣን መወገዱን ግድ የሚል መፍትሄ ብቻ ነው ሊኖር የሚችለው። ሊወጋ የመጣን ጌታዬ ቢሉት አይመለስምና ቀጥቅጦ ሊገዛ የተሰየመ ቡድን ደግሞ ዕርቅና ሰላም ቢባል መስሚያ ጆሮ የለውም። ለሥልጣን የበቃውና በአምባገነንነት የተሰየመው የሕዝብን ፍላጎትና ድምፅ ረግጦ ነውና የመነጋገሪያው መጀመሪያ እንማማር ሳይሆን፥ ሥልጣን ልቀቅ መሆኑ የግድ ይሆናል። ለዚህም ነው የወያኔ አገዛዝ ዕርቅ ከፈለገ ከሥልጣን ወርዶ ለሕዝብ ሥልጣንን ማስረከብ የሚኖርበት። ሕዝብም ከወያኔ ቡድን ልታረቅ የሚል ከሆነ በቅድሚያ የሥልጣን ባለቤት መሆን እንዳለበት ሊዘነጋ አይገባም። አለበለዚያ ነገሮች ቀይዶ በያዛቸው ብልሽትሽት ውስጥ እንዳሉና ግጭቱና ቅራኔው እየነደደ ባለበት ብሔራዊ ዕርቅ ብሎ መነሳቱ ጋሪውን ከፈረሱ ማስቀደም ሆኖ ውጤት አልባ ይሆናል።*

*ሰላምና ዕርቅን ስለፈለግነው ብቻም የሚሆን ጉዳይ አይደለም። ቅራኔውና ችግሩ እየተዋደዱ ግን እክል እንዳጋጠማቸው ባልና ሚስት ችግር ሳይሆን፥ የሀገርን የነገ ዕጣና የሕዝብን ዘላቂ ጥቅምና ፍላጎት የሚመለከት ነውና፥ ግራር ስር ሰብሰብ ብሎ በዕርቅ የሚፈቱት ችግር አይደለም።*

የሕዝብ ጎራ ሰላምና ዕርቅ ስላለ ብቻም ገዢው ክፍል አደብ ገዝቶ፤ ብልህ ሆኖ ዕርቅን ይሻል ብሎ መደምደም ከራሳችንም ተመክሮ የተጣላ ግንዛቤ ይሆናል። ኢሕአፓ የመጀመሪያውን ፕሮግራም ይፋ ሲያደርግ የሕዝብ የዴሞክራሲ መብት ከተከበረ በሰላም ሊታገል እንደሚችል ገልፆ አስፍሮ ነበር። ሊታገል እንጂ ሊታረቅ እንዳልነበረም በዚያው ግልፅ ነበር። ያገኘው ምላሽ ግን ነፃ እርምጃንና ቀይ ሽብርን ስለነበር፥ የግድ ወደ ብረት ማንሳት ተገፍቷል። ከወያኔ ጋር ገና አሸባሪው ቡድን ለሥልጣን ሳይበቃ በሽግግር መንግሥት ጥያቄ፤ በብሔረሰብ ጥያቄ፤ በዴሞክራሲ ጥያቄ ወዘተ ብዙ ክርክሮችን ኢሕአፓ አካሂዶ የነበር ቢሆንም፥ ወያኔ ለሥልጣን ሲበቃና የኢሕአፓ መሪዎችና አንጋፋ አባላትም በእጁ ወድቀው ደብዛቸው ሲጠፋ እንደዚሁ በሰላም ሊታገል (ሊታገል እንጂ ሊታረቅ አልነበረም እንደገና) ዝግጁ መሆኑን ገልጦ ነበር። ለዚህም ምላሹ እምቢ መሆኑ ያው ሕዝብ የሚያውቀው ነው። በሰላም ሊታገሉ የተነሱትንም ድርጅቶች እንዲሁ አጥቅቶና አመራራቸውን አስሮና ገድሎ፤ ነፃ ጋዜጠኞችንና የሙያ ማኅበራት መሪዎችንም አዋክቦና አግዶ ማንነቱን ለተጠራጠሩትም ሳይቀር አረጋገጠ ። ጊዜ እንስጠው ላሉትም ክፉ አውሬን መልመጃ ጊዜ መስጠት ጥፋት መሆኑን አሳያቸው። ዓመት በዓመት እየተተካ በወያኔ አገዛዝ ስር የኢትዮጲያ ሰቆቃ ሲባባስ የማያዛልቅ ፀሎት ለቅስፈት ቢሆንም በእንሞክረው የተገባበት የግንቦት 1997 ቱ ምርጫ የወያኔን ሽንፈት አብስሮ በዚያውም ይህ አሸባሪ ቡድን በሰላም ሥልጣን እንደማይለቅ ለአንዴም ለሁሌም የብዙ ሰማዕትን ደም ግብር ጠይቆ አረጋገጠ። ሰላም ሰላም ማለቱ የማያዋጣና የማይሰራ መሆኑንም ዳግም አሳየ።

ለሁሉም ጊዜ አለው እንደሚባለው የትግል መፈክርና ስልትም ሁሉም ጊዜውን ጠብቆና ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር ተዛምዶና ሰምሮ በሥራ ይውላል እንጂ አንዴ ተብሏልና ተደርጎ ነበርና በሚል ሁሌም ተግባራዊ ካልሆነ አይባልም። መፈክር ከተጨባጩ ሁኔታ አብሮ ካልሄደ የሚስተጋባ አይሆንም። የዕርቁ እውንነት ሊኖር በማይችልበት፥ ዕርቅ ብሎ መጮሁ የሚታገለውን ማደናገር ይሆናል። የሰላሙ መንገድ ከተዘጋ በኋላም በሰላም መታገል የሚለውን መፈክር ማቀንቀኑ ትግልን ግራ ለማጋባትና ታጋዩን ለወያኔ ምት ከማጋለጥ ሌላ የሚጠቅመው ነገር የለም። ሰላማዊ ትግል ተግባራዊ ሆኖ ከሕዝብ ሥነ ልቦና ጋር ተዋህዶ ሊጠናከር ቢችል ኖሮ ዛሬ በጥያቄው ላይ ትችትም ክርክርም ባላስፈለገ ነበር። የሰላማዊ ትግል ይዘት፤ አንደምታና ውጤት ተደጋግሞ ቢነገርም በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የሕዝብን ትግል በመጀመሪያ ደረጃ ገልጦ ውጤትን አስገኝቶ ለድል ሊያበቃ አልቻለም። የግንቦቱ 97 ምርጫ ውጤት በጠራራ ፀሀይ ሲዘረፍም ሕይወት ቢገበርም ሌባውን ማስቆሙ አልተቻለም። በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰላማዊ ትግል ካልሆነ ሌላው ስልት ማለትም የትጥቅ ትግሉ ጊዜ አልፎበታል፤ ተቃውሞ ያጋጥመዋል የሚባለውን ስናይ ደግሞ በተጨባጭ ተከስቶ ያለው ተቃራኒው ሆኖ እናገኘዋለን። እየተከበረና እየተደመጠ ያለው ሰላማዊ ትግል የሚለውን ትቶ ብረት ያነሳው ብቻ ሳይሆን ይባስ ብሎ ብረት አንስቶ ልክ እንደ አገዛዙ ሕዝብን የሚበድለውም መሆኑን ከዩጋንዳ፤ ከሶማሊያ፤ ኢትዮጵያ፤ ቻድና ከሌሎችም ተመክሮዎች የምናየው ነው። በሰላም ኡኡታን ማቅለጥ፤ ማዳም ራይስና ፕሬዚዳንት ቡሽ ረሳችሁን ብሎ የአሜሪካንን ሰንደቅ ዓላማ ይዞ መሰለፍ--ማልቀሱ፤ የገዢውን

ቡድን የሌለ ህሊና ለመቀስቀስ መጨመቱና ተለጣፊነትንም ለመሸከም መጎንበሱ ሁሉ ውርደትን እንጂ የሰዎቹን ጆሮ አላመጣልንም። ለሚሰግድላቸው የሚራሩ ገዢዎችና የባዕድ ኃይሎች ገና አልተፈጠሩምና ጊዜ ያለፈበትን ወይ ተሞክሮ የከሸፈን መፈክርና ስልት አንግቦ ስርየትን መሻቱ ዋልድባ ገብቶ ልጩህን ፈልጎ ይመስላል። ባለፉት 17 ዓመታት የወያኔ አገዛዝ ዕርቅና ሰላም ጠላቶቹ መሆናቸው የተረጋገጠ በመሆኑ በመጪው ምርጫ ለመሳተፍ ጎንበስ ጎንበሱ ሆነ በአቋራጭ ሂደት የሕዝብን የድል ጉዞ በመኃል ለማስቀረት ማሴሩ ፍሬ አይኖረውም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅራኔው መለስ ዜናዊ ከተባለው የሰው ዲያብሎስ ጋር ብቻ ወይም ከጭፍሮቹ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሥርዓቱ ጋር በመሆኑ በዚህም ሆነ በዚያም መንገድ አረመኔውን አስወግዶ ሥርዓቱን ማስቀጠል ከሚለው ሴራ አንፃር መቀየር ያለበት ጉልቻው ሳይሆን ወጥ ሠሪው ነውና መለስን ማስወገዱ ብቻ ያውም ሊሳካ ከቻለ፥ የገለማውን ሥርዓት አያድሰውም። ለዚህም ነው ግለሰቡን አግልሎ ከጨቋኙ ሥርዓት ጋር መታረቅ የማይቻለው። በተለይም የዚሁ ሥርዓት የመጀመሪያ አራማጆች ዛሬ የተቃዋሚን ለምድ ለብሰው የነጋበትን ከምሽት ለማድረስ ሲጥሩ ሕዝብ የሚታለል መሆን የለበትም። የሰይጣንን አመጣጥ የማያውቅ አይመንኩስ ነውና ትላንት ራሱን የትግራይ ነፃ አውጪ ሲል ባጅቶ ብዙ ሕዝብን ለማደናገር የኢሕአዴግን ጭምብል አጥልቆ ጉዳት እንዳደረሰው ሁሉ፥ ዛሬ ደግሞ ወያኔ ኢሕአዴግ ማንነቱ ከቶም የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እንኳን ሳይለወጥ በሰዎች ለውጥ ብቻ ያለፈው አበቃ አከተመ ብሎ ሊያሳምነን መነሳቱን ማወቅ ያስፈልጋል። ለዚህም ርኩስ ግቡ ይረዳው ዘንድ የሰላም ትግል ጠበቃ ሆኖ ጦርነት ሰልችቶናል በሉ በሚል መለፈፉና ማስለፈፉን ተያይዞታል። በግፍ መገደልና መሞት፣ በጭቆና ስር መማቀቅ የሰለቸው ሕዝብ ግን ጆሮ እንደማይሰጣቸው ከወዲሁ ግልፅ ቢሆንም ነብር ለፍየል ተቻችሎ መኖርን ሲሰብክ ስንሰማ የመጀመሪያችን ሊሆን አይችልም። የወያኔ አገዛዝ ወደ መቃብሩ ጉዞ መጀመሩን ራሱ ተገንዝቧልና ሥርዓቱን ለማዳን ግለሰብን ማስወገድ የሚለውን ለመሞከርና ያው ጠባብ የበላይነቱን ዕድሜ ሰጥቶ ለመቀጠል ተነስቷል። በዚህ ሴራው የሚያጅቡትና ቀዳሚ ተዋናይ የሚሆኑት ላይ ታች ሲሉ በሌላ በኩል ደግሞ አጫፋሪዎችን እያባባለ ተቃዋሚዎችን ደግሞ የክፍፍል መርዙን እየረጫቸው ነው። ከመቸውም ጊዜ ነቅቶ መታገልና ሐቀኛ ሀገር ወዳዶች ተሰባስበው ፀረ ወያኔን ትግል የሚያፋፍሙበትን ዘዴ መትለም ያሻል። ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር ነውና አስፈላጊ የሆነውን ትግል ከማካሄድ አንፃር ጋሬጣ የሆነውን ሁኔታ ሁሉ ማቸነፍ የሚገባና የሚቻል መሆኑንም መዘንጋት የለበትም።

ዝንጅሮ ሲበዛ ይወረዛል ገደል፥
ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል።

የተባለውን ስናስታውስ ደገሞ ለትዕግስትም ልክ እንዳለው ተገንዝበን የመሸፈትና የግመፅ ግዴታችንን እንወጣለን ማለት ነው። የሰው ልጅ ሰብዕና ያለው ፍጡር እንደመሆኑ መጠን ሊሸከመው የሚችለው ግፍና በደል ወሰን የለሽ፣ ልክ የለሽ ሊሆን አይችልም። በቃኝ አሻፈረኝ

ብሎ መሸፈት ማመፅ ግዴታው ሆኖ ከፊቱ የሚደቀንበት ወቅት አለ። ያኔ ከዚህ ግዴታው ለማምለጥ ቢሞክር ራሱን ለማያባራ መከራ አጋልጦ ጭቁንነቱን በፀጋ ተቀብሏል ማለት ነው። ትዕግስተኛ ከፈለገበት ይደርሳል የሚለው አነገጋር ጋር በደፈናው ጠብ ባይኖረንም፥ ጭቆናን በትዕግስት ማስተናገዱ ለሕዝብ መብት መከበርና ከጭቆና መላቀቅ የሚበጅ መንገድ አይደለም። ነፃነትን ፈልጎ ለጭቆና ትዕግስት ማጣቱ በጎና ተገቢ አቋም ነው። በሰበብ አስባቡ ህሊናና ወኔን እየቆነጠጡ፤ ውርደትን በውርደት ላይ እያስተናገዱ ከመሞት መሰንበት በሚል ፈሊጥ ብቻ ለጭቆና ተገዢ ሆኖ ቀን ተቀንን ማስተናገዱ የኩሩ ዜጋ መለያ አይደለም። እምቢኝ ብሎ ለመነሳት ደግሞ የአመፁ መጨረሻ ምን ይሆናል ከሚል ብቻ የሚወሰን ሊሆን አይችልም። በዘመናዊ መሳሪያ ታጥቆና በፈረንጅ ዕብሪት ተወጥሮ ኢትዮጵያን የወረረውን የጣሊያን ጦር የተጋፈጡት አርበኞች ዛሬ አስታራቂ ሽማግሌዎች ብለው ራሳቸውን ሰይመው "አትችሉትምና ለወያኔ ስገዱ" እንደሚሉት ይህን ጠላት አንችለውም ብለውም በቅኝ ገዥዎች መገዛትን ተቀብለው ቢሆን ኖሮ፥ የኢትዮጵያ ዕጣና ሁኔታ ከዛሬው በከፋ ነበር። ከሁሉም በላይ ውርደቱና በጨቋኝ-- ሀገር በቀል ሆነ ባዕድ-- መረገጡ አለ ። ይህን መቀበል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክና መለያ አይደለምና በፏለለ ሀገር አጥፊ ቡድን ላይ መነሳት፤መሸፈት፤ ማመፅ፥ ቀነ-ቀጠሮ ሊሰጠው የማይገባ ግዳጅቻን ነው።

የበደሉ ክምር ጫንቃ ከሚቸለው በላይ ሲሆን፤ ሀገር ለአሻበሪ ቡድንና ለባዕዳን መሳለቂያ ሆና ስትዋረድ የማመፅ ደወል ማቃጨሉ አይቀሬ ነው። ይህን የማይሰማ ጆሮ ደግሞ ዕዳው የራሱ ነው። የወያኔ አገዛዝ በምንም ዓይነትና ሁኔታ የሕዝብን ድምፅ የሚሰማ ሆነ የሚያከብር አይደለም። የአገዛዙን ዕድሜ ለማራዘም አሰመሳይ ለውጦችን ሊያደርግ ይችላል። ጨረቅና ማዘቢያ ያለውን ሰንደቅ ዓላማ ምናምንቴ ቢለጥፍበትም አከብረዋለሁ ብሎ ሊመፃደቅ ይችላል። ኢትዮጵያ ሲሉት ያጓራ የነበረው አምባገነንም ይሁንላችሁ ብሎ ሸማውን ሊለብስ ይችላል። ኢትዮጵያዊነት ልብ ወልድ ነው ሲል የከረመውን ዘንገት ያደረገ መስሎ የኢትዮጵያዊነት ዋና ጠበቃ ነኝ ብሎ ሊሞካሽም ይችላል። ይህ ሁሉ ግን ከአንገት በላይ ነው። የልቡን እየሰራ በአፋዊ ደረጃ፤ በላባ ክብደት ደረጃ የሚያስተናግደው ማደናገሪያ ነው። አሳሳች ካለይ ሲሉት ከታች ነውና ማወናበጂያ እርምጃው ነው። መቶ እስረኛ ሲለቅ ሺውን አጉሮ ያሰቃያል። ነፃ ጋዜጠኞችን ከእስር ሲለቅ የማተም መብታቸውን ያግዳል። ለአንድ የፀና ወይም አንገራጋሪ ተቃዋሚ በደርዘን ተፃራሪ ተለጣፊና አንጃ ይቀፍቅፋል፤ያቅፋል። ለክልሉ ሁሌም ፀንቶ ይታገላል፥ ማለትም ደደቢት ከሰፈረበት የጠባብነት ዛር የሚያላቅቀው ጠበል ገና አልተረጨበትም። የወያኔ አገዛዝ ቢጨምት እስኪጨመድድ ነውና ከዚህ ማንነቱን ለመለወጥ ካለመቻሉ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዓመታት ሲታገልላቸው የቆዩ ዋና ዋና ጥያቄዎቹ--ከመሬት ለአራሹ እስከ እኩልነትና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር-- አሁንም በሚያረካው ደረጃ ቀርቶ በመለስተኛ ደረጃም ቢሆን አልተመለሱለትም። በአጭሩ የጭቆናና ግፉ ዋንጫ ሞልቶ እየፈሰሰ ነውና የዛሬው ካለፈው ይከፋል ወይስ ይቀንሳል በሚል ፋይዳ ቢስና ጉንጭ አልፋ ክርክር ሕዝብ ሊጠመድና ዱሮ ክፉ

ነበር በሚል የዛሬውን አረመኔ ሊሸከም አይጠበቅም፡፡ መሸፈት ማመፅ ዛሬም የግድ ሆኖበታል ማለት ነው፡፡

አመፅ ሲሉ አመፅ ስንል በሚል ጳግም በይፋ መፃፉ አስፈላጊ ባይሆንም መብትን ለማስከበር ሕዝብ ተንስቶና የአገዛዙን ማደናገሪያዎች ሁሉ ሰባብሮ ጥሎ መገኘቱ ወሳኝና መደረግ ያለበት መሆኑን ስንቀበል በአንፃሩ ደግሞ ለስልትም ስልት መኖሩን የምንስት ሊሆን አይገባም፡፡ ኮሶን በኮሶ ነውና አገዛዙን በሰላም ታግሎ ማሸነፉ የሚያስኬድ ባለመሆኑና አገዛዙ ራሱ ሕዝብን ወደ አመፅ በግድ በመግፋቱ መፍትኄው ሁለገቡን ትግል እውን ለማድረግ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በማለቂያውና በሥርዓቱ መቀበሪያ ጊዜ ይህን አገዛዝ በዕድሜ መራዘም ሴራው ለማጀብ የሚሸቀዳደሙትን ታሪክ የሚስቅባቸው ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ይህ ቅሌት የሕዝብ ሊሆን አይቸልምና ሕዝብ የአመፅን ጎዳና በተደራጀና በቆረጠ መልክ መያያዝ ይኖርበታል፡፡ ካለፉት ሙከራዎችና ተመክሮዎች በመማርና የጠላቱን ማንነት ጠንቅቆ በመረዳት አመፁን በየፈርጁ አደራጅቶ ፀረ ሕዝቡን አገዛዝ በተባበረ ትግል ከማስወገድ ሌላ ምንም አማራጭ የለውም፡፡ ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል!!

## የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግሉ ድልን ይቀዳጃል!